June 02, 2022
ግንቦት፣ 2014 ዓ/ም

# “ለብአዴን የአንድ ቀን እድሜ መፍቀድ አማራ ጠፍቶ ኢትዮጵያ ፈርሳ ማየትን መፍቀድ ነው”

## ከአማራ ሕዝባዊ ሃይል/ፋኖ/ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ።

የዛሬ 31 ዓመት በውጭ ፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎች እገዛ ኢትዮጵያን የተቆጣጠሩት ትህነግና ኦነግ፣ አማራ ያልሆኑና በአማራ ጥላቻ የሰከሩ አማርኛ ተናጋሪ ግለሰቦቸን በመሰብሰብ ብአዴን የሚባል ፀረ አማራ አደረጃጀት ፈጠሩ። ያለአማራው ሁነኛ ተሳትፎ የተፈጠረው ብአዴን በአማራው ማህበረሰብ ላይ ከተጫነ በኋላ የሆነኝ ብሎ አማራው የራሱን አደረጃጀት እንዳይፈጥር፤ የደህንነትና የኢኮኖሚ ተቋሞችን እንዳይገነባና እራሱን ከታቀደለት የመጥፋት እቅድ እንዳይከላከል በማድረጉ ዛሬ ላይ ለሚፈፀምበት የተቀነባበረ የዘር ማጥፋት ፍጅትና የመሬት ወረራ ተጋላጭ አድርጎታል። ከ31 ዓመት በፊት የታቀደው ወንጀል ዛሬ በፌደራል መንግሥት ተብዬው አዛዥነት በብአዴን ፈጻሚነት በአማራው ሕዝብ ላይ በራሱ ክልል ውስጥ በስፋት እየተፈጸመበት ይገኛል።

የዛሬ ሦስት ዓመት ጀግናውና ትንቢተኛው ጀኔራል አሳምነው ፅጌ ያስተላለፈው የማስጠንቀቂያ መልእክት ወይም የማንቂያ ደወል በአማራው እንዝህላልነት ስላልተተገበረ ዛሬ የኦሮሙማ ተስፋፊዎች በ16ኛ መቶ ክፍለዘመን የተፈጸመውን ወረራ እና እልቂት እንደገና ለመተግበር ሰፊ ዝግጅታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ከገቡ ዋል አደር ብለዋል። የጀኔራል አሳምነው ፅጌን ማስተንቀቂያ ሰምቶ ሕዝቡ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጎ ቢሆን ኖሮ በኦነጋዊው አብይ አህመድና በፀረ አማራው ብአዴን ቅንጅት በወገናችን ላይ ዛሬ በመፈፀም ለይ ያለው ግፍ በተቀለበሰ ነበር።

ዛሬ በአማራው ላይ የአማራን ክልል ጨምሮ በሃገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚፈጸመው ግፍ ከዘር ማጥፋት ጋር የተያያዘ ነው። የአማራን ማህበረሰብ መሪ አልባ ለማድረግ ብአዴንና አብይ አህመድ የበቁ ስመ ጥር የአማራ ምሁሮችን፣ የእምነት አባቶችን፣ የጦር ማኮንኖችን፣ ፋኖ አርበኞችን፣ አክቲቪስቶችን፣ ጋዜጠኞችን እና ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን ውሃ በማይቋጥር ምክንያት መያዝ የሚችለውን ያለፍርድ ቤት እውቅና በማሠር፣ የማይችለውን አሳዶ በመግደል፣ ከሥራ በማገድ ቤተሰቡን ለረሃብ በማጋለጥና ትውልድ ተረካቢ ተማሪዎችን በመረሸን የትውልድ ቅብብሎሽን ለማቋረጥ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በሕወሃት ዘመን የተጀመረውን አማራን በፖሊሲ ደረጃ አዳክሞ መሪ አልባ ማድረግን የዛሬ ተረኛ የኦሮሙማ መንግሥት ቀጥሎበታል። ስለሆነም አማራው ከኢኮነሚው፣ ከፓለቲካው፣ ከመከላከያና ከደህንነቱ በገፍ እየተባረረ ይገኛል። “የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ በኦሮሚያ ክልል ከ1800 ብር በታች የሚሸጠው ማዳበሪያ የአማራውን ገበሬ 5000 ብር በመክፈል እንዲገዛ ካደረጉት በኋላ ሰሞኑን የአማራን ክልል ገበሬ እርሻውን ማረስ ባለበት ወቅት ጠብቀው ለቀጣይ ረሃብ፣ በሽታና ተዛማጅ ችግሮች እንዲጋለጥ “የሕግን የበላይነት ለማስከበር” በሚል ሽፋን ሰፊ ዘመቻ ከፍተውበታል።

በአሁኑ ሰዓት በብአዴን መሪነት፣ በከሃዲው ጀኔራል አበባው ታደሰ የበላይ አስተባባሪነት የአማራ ክልል ልዩ ሃይል ዩኒፎርም የለበሱ የኦነግ ሃይሎች በሙሉ ሀይላቸው በብአዴን የቀበሌና የወረዳ አመራሮች መረጃና ድጋፍ ሰጭነት በአማራ ክልል በዋናነት በጎጃምና በቤተ አማራ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየፈፀሙ ይገኛሉ። የዚህ ዘመቻና ጭፍጨፋ መዳረሻ ግቡ ኦሮሚያ የሚባል አገር ለመመሥረት ስለሆነ ይህ ፀረ-ኢትዮጵያ ወንጀል አድማሱን በማስፋት በሲዳማ፣ በጌዲዮና በሌሎች የደቡብ ክልል ብሔሮች ላይ እንደሚፋፀም ሳይታለም የተፈታ ነው።

**ስለሆነም ለአማራ ሕዝብና ለመላው አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚከተለው የትግል ጥሪ እናቀርባለን፡-**

ለብአዴን የአንድ ቀን እድሜ መፍቀድ እራስን በራስ ማጥፋት መሆኑን ተገንዝበህ ከብአዴን የፀዳ ቀበሌና ወረዳ ፍጠር ጠላትህ አሁን የሚፋጽመውን ጭፍጨፋና ማሳደድ ለመሸፈን ተቀርቋሪ ለመምሰል ትራክተር በፎቶ እያሳየህ ነው። ቀደም ሲል ግን ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ከልክሎሃል። ስለሆነም በዚህ የማጭበርበሪያ ወጥመድ ውስጥ እንዳትገባ በመጠንቀቅ በዚህ ሴራ ላይ በሚሳተፉት አቀንቃኞች ላይ ትምህርታዊ እርምጃ በመውሰድ ህልውናህን አስከብር!
ሕወሃትና አብይ አህመድ የሚመራው የከሃዲዎች ስብስብ ሃገሪቷን ሲያፈርሷት የበይ ተመልካች መሆን እንደለለብህ ላንተ ማስታወስ ያለብን አይመስለንም። ስለሆነም እነዚህ አገር አጥፊዎች ይህ እኩይ ዓላማቸው የሚሳካላቸው ከሆነ እሜዳ ላይ እንዳትቀር የራስህን አፅመ ርስት ዳር ድንበር ለማስከበር ከአሁኑ ተዘጋጅ!

አንተን እየሰለለና ከላይ የመጣ ትእዛዝ ነው በማለት የሚያስርህን፣ የሚያሳድድህንና ጨፍጭፎ ለጨፍጫፊ የሚሰጥህን በቀበሌህና በወረዳህ አብሮህ የሚኖረውን የአገዛዙን አገልጋይ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ምን ማለት እንደሆነ በተግባር በራሱ ላይ ማሳየት ጀምር፣ ዛሬ መከራህን የሚያሳይህ የኑሮ ውድነት የተከሰተው አንተን በማሽመድመድ ህልውናህን ለመፈታተን ብሎም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ በዘረኛው የአብይ አህመድ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ የተቀረፀ መሆኑን አትርሳ! አንተን በተለይ እንደአማራ እንድትጠፋ ማድረግ የዚህ ፖሊሲ ማዕከል ስለሆነ የምታደርገው ሕዝባዊ እምቢተኝናት ለጥገና ሳይሆን ለየአማራ ህልውና በፋኖ ክንድ ይከበራል!

ሥር ነቀል ለውጥ መሆን ስላለበት ለረጅም የትግል ጊዜ ተዘጋጅ!
የአማራ ሕዝባዊ ሃይል/ፋኖ/ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ

ግንቦት፣ 26 ቀን 2014 ዓ/ም